VLUCHTELINGENWERK VLAANDEREN

## በጥገኝነት ጠያቂዎች ላይ ያለው ተጽእኖ ምንድነው?

አዲሱ የቤልጂየም ፌደራል መንግስት በጥር 31, 2025 ስራ ጀምሯል። ይህ መንግስት በጥገኝነት እና በስደት ላይ አዳዲስ ፖሊሲዎችን ኣቅርቧል። መንግሥት በጥገኝነት እና በስደት ላይ ጥብቅ ሕጎችን ማውጣት እንደሚፈልግ በመገናኛ ብዙኃን ጠቁሟል። በቅርቡ ቤልጂየም ከመጣህ ይሄ ለውጥ የተወሰነ ስጋት ሊፈጥርብህ ይችላል። ይህ በራሪ ጽሁፍ እነዚህን እቅዶች ለማብራራት እና ስለ ተጽኖአቸው ለእርስዎ ለማሳወቅ የተጻፈ ነው።

የመንግሥት ስምምነቶች፣ የመንግስቱ **የወደፊት ዕቅዶች የያዙ እንደሆኑ ልብ ማለት ያስፈልጋል።** እቅዶቹ ወደፊት ምን እንደሚያመጣ የሚጠቁሙ ናቸው, ነገር ግን እስካሁን ድረስ ተግባራዊ ኣልሆኑም፣ እነዚህ ዕቅዶች ውጤት እንዲኖራቸው **ወደ ሕጎች መቀየር አለባቸው** ። ይህ ሂደት **ብዙ ወራት ወይም ዓመታት ሊወስድ ይችላል** .

Infolijn

ይህንን በራሪ ጽሁፍ ካነበቡ በኋላ ማንኛቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን የእኛን የመረጃ መስመር (ስልክ፣ ዋትስአፕ፣ ቴሌግራም እና ኢሜል) https://vluchtelingenwerk.be/infolijn **ያግኙ** ወይም ጠበቃዎን ያግኙ።

## በጥገኝነት ጠያቂዎች ላይ ያለው ተጽእኖ ምንድነው?

- **የጥገኝነት ሂደቱን የበለጠ ጥብቅ ማድረግ ይፈልጋል** ። ጥገኝነት ጠያቂዎችን እንደ ሞባይል እና ላፕቶፕ የመሳሰሉ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎቻቸውን እንዲያስረክቡ ማስገደድ ይፈልጋሉ። ጥገኝነት አገልግሎቱ እውነትን እየተናገርክ እንደሆነ ለማረጋገጥ በእነዚህ ፍተሻዎች ማለፍ ይፈልጋል።
- መንግስት ሰዎች በቤልጂየም ወይም በተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት ለጥገኝነት ደጋግመው እንዲጠይቁ አይፈልግም። ወደፊት ይህን የሚያደርጉ ሰዎች መጠለያ አይሰጣቸውም።
- የ ይግባኝ ጊዜው **በተቻለ መጠን አጭር ይሆናል።** የይግባኝ ሂደት ኣንድን ስደተኛ በፈቃደኝነት ወደነበረበት ሃገር የመመለስ ሂደቱን አያቆምም። ይህ ማለት እርስዎ የ ይግባኝ ውሳኔን በመጠባበቅ ላይ ሳሉም ቢሆን መንግሥት ከመመለሻዎ ጋር እንዲተባበሩ ይፈልጋል።
- መንግሥት የጥገኝነት ጠያቂውን ‘የአቀባበል ቀውስ/ የመጠለያ ሽግር ’ በተቻለ ፍጥነት መፍታት ይፈልጋል። እስከዚያ ጊዜ ድረስ ተጋላጭ ለሆኑ ጥገኝነት ጠያቂዎች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል። ይህ ማለት **የ ላጤ/ነጠላ ወንዶች በመጠበቂያ ዝርዝር መቆየት ሂደት**

**አሁንም ተግባራዊ ይሆናል** ፣ እና ነጠላ ወንዶች ጥገኝነት በሚጠይቁበት ቀን መጠለያ አይሰጣቸውም።

- በቤልጂየም ውስጥ የጥገኝነት ጠያቂዎች ቁጥር እያነሰ ሲመጣ መንግሥት የመስተንግዶ ማዕከሎችን መዝጋት ይፈልጋል። በሆቴሎች ውስጥ ያሉ የግል ቦታዎች እና የድንገተኛ አደጋ መጠለያዎች ይዘጋሉ።. **የመቀበያ አውታር የበለጠ መሠረታዊ ይሆናል።** በትልልቅ መጠለያዎች ውስጥ፣ እንደ ምግብ እና መኖሪያ ያሉ ቁሳዊ እርዳታ ብቻ ያገኛሉ። የራስዎን ምግብ ለመግዛት ከአሁን በኋላ የኪስ ገንዘብ ማግኘት አይችሉም።

## አዎንታዊ ውሳኔ ባገኙ ሰዎች ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል?

መንግሥት በአብዛኛው ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ መስጠት ይፈልጋል። ይህ **ንዑስ ጥበቃ/ግዚያዊ ጥበቃ ተብሎ ይጠራል።** ይህ ሁኔታ እውቅና ከተሰጠው ስደተኛ በደረጃ ያነሱ መብቶችን ይሰጣል። ስለዚህ የቤተሰብ መገናኘት ሂደቱ የበለጠ አስቸጋሪ ይሆናል፣ እና ማህበራዊ እርዳታ (leefloon) ተደራሽነቱ ያነሰ ይሆናል።

**ዕውቅና ያላቸው ስደተኞች** ያለ ገቢ እና መኖሪያ-ቤት **ቤተሰብ ለመቀላቀል** ለማመልከት ስድስት ወራት ይኖራቸዋል ። ማህበራዊ እርዳታን ለማግኘት የውህደት ኮርስ መከተል ይኖርብዎታል።
**የንዑስ/ግዚያዊ ጥበቃ ያላቸው ሰዎች የቤተሰብን መቀላቀል** ከመጀመራቸው በፊት ሁለት ዓመት መጠበቅ አለባቸው ። ዝቅተኛ ወርሃዊ ገቢ 2.227 ዩሮ እና ለአንድ ልጅ 228 ዩሮ ሲጨመርላቸው ሊኖራቸው ይገባል። ይህ የቤተሰብ መገናኘትን ማከናወን ለሚፈልጉ ላልደረሱ ታዳጊዎች አይተገበርም። በቤልጂየም እና በትውልድ ሀገር ውስጥ ያለ ሰው የቋንቋ እና የዜግነት ፈተና ማለፍ አለበት.
**ንዑስ ወይም ጊዜያዊ ጥበቃ ያላቸው ሰዎች** አወንታዊ ውሳኔ ካገኙ በኋላ በመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት ውስጥ **የማህበራዊ ድጋፍ ኣያገኙም** ። በውህደት ጥረታቸው ላይ በመመስረት ሌሎች የማህበራዊ እርዳታ ዓይነቶችን ያገኛሉ። እነዚ ማህበራዊ እርዳታ ምን ኣይነት እንደሚሆኑ አናውቅም።

B-**ካርድ ለማግኘት አስቸጋሪ** ይሆናል ። ብዙ መስፈርቶችን ማሟላት አለብዎት;

- በቋንቋ እና በዜግነት ፈተናዎች ማለፍ።
- የA-ካርድዎን ሲቀበሉ የሚመለከተውን መስፈርት ያሟሉ።
- ለሀገር ደህንነትና ለህዝብ ሰላም ስጋት አትሁኑ።
- የአስተዳደር ክፍያዎች መክፈል።
- እራስን መቻል ማህበራዊ ፣እርዳታን አይጠቀሙ።

**የቤልጂየም ዜግነት ማግኘት** የበለጠ ከባድ ይሆናል። €1,000 ያስወጣል እና የቋንቋ እና የዜግነት ፈተና ማለፍ አለበት።

## ሰነድ በሌላቸው ስደተኞች ላይ ምን ተጽእኖ አለው?

- **ለሁሉም የሚሰራ ፍቃድ ኣሰጣጥ ሂደት**/collective regularization **አይኖርም** . ይህ ማለት ሰነድ የሌላቸው ስደተኞች ሰነዶቻቸውን የሚያወጡበት አጠቃላይ ሥርዓት አይኖርም ማለት ነው። በልዩ ሁኔታ ለአንድ ሰው የመኖሪያ ፈቃድ እንዲሰጥ የሚፈቀደው ኣካል የኢሚግሬሽን ቢሮ ብቻ ነው።
- ክልሉን ለቀው እንዲወጡ የታዘዙ ሰዎች **ወደ ሀገራቸው የመመለሱን ስምምነት መፈረም ይጠበቅባቸዋል** ። ይህ ማለት በፈቃዳቸው የመመለስ ሂደቱ መተባበር አለባቸው ማለት ነው። ወድያውኑ መመለስ ካልተቻለ በየጊዜው ወደ ባለሥልጣኖቹ መቅረብ አለባቸው። ይሄን የማያከብሩ, ተይዘው ወደ ዝግ ማእከል ሊወሰዱ ይችላሉ.
- ልጆች የያዙ ቤተሰቦች ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት አይታሰሩም .
- **ፖሊስ** ወደ ቤትዎ ሊገባ ይችላል። ይህ ሊሆን የሚችለው ለብሔራዊ ደኅንነት ወይም ለሕዝብ ደኅንነት ሥጋት ከሆኑና ለመርማሪው ዳኛ ፈቃድ ከሰጡ ብቻ ነው።
- **ድንገተኛ የሕክምና እንክብካቤ ማግኘት የበለጠ አስቸጋሪ ይሆናል።** መንግስት በዶክተሮች እና በሆስፒታሎች ላይ ጫና ይፈጥራል, ነገር ግን የድንገተኛ ህክምና የማግኘት መሰረታዊ መብት ይቀጥላል። ሆኖም ዛሬ በነጻ የሚያገኙዋቸው ለአንዳንድ የሕክምና ወጪዎች እራስዎ መክፈል ሊኖርብዎ ይችላል።